# ምድብ አራት (ከ7ኛ — 9ኛ) ክፍል
## 32 ኛ ሳምንት
## ጰንጤቆስጤ

**ዓላማ**

- በ50ኛው ቀን ስለተሠጠው የመንፈስቅዱስ ሥጦታና በአንድ ልብ ስለመሰብሰብ ጥቅም መማር፡፡

**የሚጠና ጥቅስ**

- ***"ሁሉም በአንድ ልብ ሆነው አብረው ሳሉ፡፡"*** የሐዋ.ሥ. 2፣1

**ምንባብ**

- የሐዋ.ሥራ 2

**መግቢያ**

- ጰንጠቆስጤ 50ኛው ቀን ማለት ነው፡፡120ው የክርስቶስ ቤተሰቦች (12 ሐዋርያት፣72ቱ አርድዕትና 36ቱ ቅዱሳት እንስት) እመቤታችን ባለችበት መንፈስቅዱስን የተቀበሉበት ዕለት ጰንጠቆስጤ ይባላል፡፡
- ምክንያቱም መንፈስቅዱስን የተቀበሉበት ዕለት ክርስቶስ በተነሣ በ50ኛው ቀን ነበርና ነው፡፡
- በዛሬው ትምህርታችን የጰንጠቆስጤ ቀን ታሪክ እና የሐዋርያትን አገልግሎት አጀማመር እናያለን፡፡

**ትምህርቱ**

- ክርስቶስ በተነሣ በ50ኛው ቀን ባረገም በ10ኛው ቀን ደቀመዛሙርቱ በማርቆስ እናት ቤት ተሰብስበው ነበር፡፡እመቤታችንና ሌሎችም ከእነርሱ ጋር ነበሩ፡፡120 ያህሉም በአንድ ልብ ይጸለዩ ነበር፡፡
- በድንገትም እንደሚነጥቅ ዓውሎ ነፋስ የነበሩበትን ቤት ሞላው፡፡
- በእያንዳንዳቸውም ላይ መንፈስ ቅዱስ በእሳት ላንቃ አምሳያ ወረዳባቸው፡፡ በተለያየ ቋንቋ መናገር ጀመሩ፡፡የአይሁድን በዓለ ፋሲካ ለማክበር የተሰበሰቡና ከተለያዩ ሀገሮች የመጡ ሰዎች ነበሩ ፣ በየራሳቸው ቋንቋ ሲናገሩ ሰምተው ተደነቁ፡፡
- አንዳንዶቹ ግን የወይን ጠጅ ጠጥተዋል ብለው አጉረመረሙ፡፡ቅዱስ ጴጥሮስ ከ11ዱ ደቀመዛሙርት ጋር ተነስቶ የተሰበሰቡትን አስተማረ፡፡አሁን የሚያዩትና ከዚህ በፊት የተመለከቱት በሙሉ በነቢያት የተነገረው ትንቢት ፍጻሜ መሆኑን አስረዳቸው፡፡ ከዳዊት መዝሙርም ስለክርስቶስ ትንሣኤና ዕርገት የተነበየውን ጠቅሶ አስተማረ ምን እናድርግ ሲሉትም ***"ንስሐ ግቡ ኃጢአታችሁም ይሰረይ ዘንድ እያንዳንዳችሁ በኢየሱስ ክስቶስ ስም ተጠመቁ የመንፈስቅዱስንም ስጦታ ትቀበላላችሁ፡፡"*** አላቸው፡፡በዚህ ቀን 3000 ሕዝብ አምኖ ተጠመቀ፡፡
- ሁሉም በወንድማማችነት፣ በኅብረትና በጸሎት አንድ ልብ ሆነው መኖር ጀመሩ፡፡ ይህም ክርስቶስ ሲል የነገራቸው ፍጻሜ ነበር፡፡***"ያመኑትንም እነዚህ ምልክቶች ይከተሉኣቸዋል፣በስሜ አጋንንትን ያወጣሉ በእኛ ቋንቋ ይናገራሉ፡፡"*** ማር.16፣17-18 ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን ከተቀበሉ በኋላ፣ወንጌልን ሰበኩ፣ ስለ ክርስቶም መሠከሩ፡፡
- ዓለም አልተገባቸውምና - ታሠሩ፣ተፈዘባቸው፣ተገረፉ እነርሱ ግን በስሙ መከራ በመቀበላቸው ደስተኞች ነበሩ፡፡ እስከ ሞትም ታምነው መሰከሩለት፡፡

**የዚህ ታሪክ ጠቃሚ (አስፈላጊ) መልእክቶች**

- ጌታችን ከማረጉ በፊት ጠቃሚ ትዕዛዞችን ስጥቶአቸዋል፡-
  - (1) ***"እናንተ ግን ከላይ ኃይል እስክትለብሱ በኢየሩሳሌም ከተማ ቆዩ፡፡"*** ሉቃ. 24፣49(2)
  - (2) " " ማቴ. 28፣19-20

- ጌታችን ኢየሱስ ክስቶስ እንዳዘዛቸው ደቀመዛሙርቱ በኢየሩሳሌም ቆዩ፡፡ የተሰበሰቡት በአንድ ቤት ሲሆን በአንድ ልብ ሆነው እየጸለዩ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን ተስፋ ይጠባበቁ ነበር፡፡ትዕዛዙን ጠብቀው በአንድ ልብ ይጠብቁት ነበርና፤መንፈስ ቅዱስ ጌታ ባረገ በ10ኛው ቀን ተለከላቸው፡፡በአንድ ቤት ተሰብስበውም ጸጋ መንፈስቅዱስን ተቀበሉ በተለያየ ቋንቋ መናገርም ጀመሩ፡፡
- ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከኢየሩሳሌም ጀምሮ ምሥክሩ እንደሚሆኑ ነግሮአቸው ነበር፡፡የተሰጣቸው ተስፋ የመንፈስቅዱስን ኃይልና ጸጋ ከተቀበሉ በኋላ ሐዋርያት አገልግሎታቸውን በኢየሩሳሌም ጀመሩ በመጀመሪያው ቀንም 3000 ሺህ ሕዝብ አጠመቁ፡፡ጌታችን እንደነገራቸውም ታላላቅ ተዓምራትና ድንቆች ይከተሉአቸው ነበር፡፡

## ማጠቃለያ

- እግዚአብሔር የገባልንን ቃል ይፈጽማል፡፡ ነገር ግን ከላይ እንደተማርነው፡፡ ቃል ኪዳኑ እንዲፈጽምልን (1) ታዛዦችና (2) አንድ ልብ መሆን አለብን፤ይህም በመልካም ነገሮች በመስማማት እና በአንድ ልብ በመጸለይም ነው፡፡

## ጥያቄዎች

(1.) ጰንጠቆስጤ ምን ማለት ነው? በዚያን ጊዜ ምን ተከሰተ?

(2) ሐዋርያት ከጌታችን ዕርገት በኋላ የት ተሰበሰቡ? ስንትስ ነበሩ?

(3.) ጌታችን ካረገ ከስንት ቀናት በኋላ ነው ደቀመዛሙርቱ መንፈስ ቅዱስን የተቀበሉት ?

(4) ያመኑትን ምን ዓይነት ምልክቶች ተከተሉቸው?

(5) መንፈስቅዱስን ሲቀበሉ በምን ዓይነት ስብስብ ሆነው ነበር?

(6) በቤታችሁ ከት/ትቤት ጓደኞቻችሁ... ጋር በአንድ ልብ ትሠበሰባላችሁ?

- በእናንተ ውስጥ ያለ መንፈስ ቅዱስ ተጠምቃችሁ ቅዱሱን ቅባት (ሜሮን) ከተቀባችሁ ጊዜ አንስቶ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የነበራችሁ ግንኙነት ምንድር ነበር? ሥጋችሁ የመንፈስ ቅዱስማደሪያ እንደሆነ ቅዱሱ የእግዚአብሔር መንፈስ በውስጣችሁ አድሮ በእናንተ እንደሚሠራ ይታወቃችኋል?
- ካህኑ በሚጠቅሰው በቡራኬ ጸሎት ውስጥ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በኅብረት ትገባላችሁ?
- የእግዚአብሔር መንፈስ በሥራችሁ ውስጥ ሁሉ ተካፋይ ነውን?
- ወይስ ያለ እግዚአብሔር መንፈስ በተናጠል በገዛ አመለካከታችሁ፣ በፈቃዳችሁ፣ በማስወገዳችሁና በግል ፍላጎቶቻችሁ ነው የምትሠሩት?
- የመንፈስ ቅዱስ ሥራ በጸሎታችሁ፣ በተመስጦአችሁና በአገልግሎታችሁ ውስጥ ልዩ ኃይል ይሰጣችኋል? ለእግዚአብሔር ፣ ለቤተ ክርስቲያኑና ለመንግሥቱ በሚኖራችሁ ፍቅር ውስጥስ?
- ".. መንፈስ ይሙላባችሁ..." (ኤፌ 5፡18) የሚለውን የሐዋያውን ትእዛዝ ተግባራዊ ታደርጋላችሁ?
- "... በእናንተ የሚናገር የአባታችሁ መንፈስ ነው እንጂ የምትናገሩ እናንተ አይደላችሁም፡፡" (ማቴ 10፡20) ተብሎ እንደተናገረው ከሆነላችሁ ቃላቶቻችሁ በአድማጮቻችሁ ልብ ላይ ኃይልና ውጤት ሊያመጡ ይችላሉ፡፡
- ወይስ ራሳችሁን ችላችሁ ስለምትናገሩ ወይስ መንፈስ ቅዱስ አንደበታችሁን አይከፍትላችሁም?
- ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በገላትያ 5፡22 ላይ የጠቀሳቸው የመንፈስ ፍሬዎች በእናንት ዘንድ አሉ? እርሱ ይህን አስመልክቶ የተናገረው እንዲህ ብሎ ነው፡- "የመንፈስ ፍሬ ግን ፍቅር፣ ደስታ፣ ሰላም፣ ትእግሥት፣ ቸርነት፣ በጎነት፣ እምነት፣ የውሃት፣ ራስን መግዛት ነው፡፡" ወይ ሕይወታችሁ ምንም ፍሬ አያፈራም አሊያም የመንፈስ ፍሬዎችን ገንዘቦቻችሁ ሳታደርጉ የመንፈስ ቅዱስን ስጦታዎች ለማግኘት ትመኛላችሁ!?
- አንዳንድ ጊዜ ሊወገዱ በሚገባቸውና በእናንተ ውስጥ ከሚያድረው ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ሊስማሙ በማይችሉ አንዳንድ ነገሮች አማካይነት የእግዚአብሔርን መንፈስ ማሳዘናችሁ (ኤፌ 4፡30) ይታወቃችኋል? ለብ ባለ ሕይወትና በውስጣችሁ ለሚሠራው ለመንፈስ ቅዱስ ምላሽ ባለመስጠት መንፈስ ቅዱስን ታሳዝናላችሁ? 1ኛ ተሰ 5፡19፡፡
- ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያላችሁን የግንኙነት መጠን መላልሳችሁ ገምግሙና ራሳችሁን "ሕይወቴ መንፈሳዊ ሕይወት ነው? ቃላቶቼስ መንፈሳዊ ናቸው?" ብላችሁ ጠይቁት፡፡

ይቆየን፡፡